# እንግዶች እንኳን ደህና መጣችሁ!






- ⇒ የእሁድ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ የአርብ ፕሮግራም ይካፈላሉ?
- ⇒ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይካፈላሉ?
- ⇒ ማገልገል ይፈልጋሉ?
- ⇒ Yeec.org App ጭነዋል?
- ⇒ http://www.yeec.org/ ይጎበኛሉ?

ሽማግሌዎችን ለማግኘት:-
773-886-0818 (ወ/ም ሲሳይ)
773-507-0147 (ወ/ም ጸደቀ)
630-677-0293 (ዶ/ር ተረፈ)
773-910-0486 (እ/ት ሰናይት)
773-556-5345 (ወ/ም ረድኤቱ)

**መደበኛ ፕሮግራሞች**
እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.
አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m.

| የችካጎ የምስራች ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን | | Chicago Yemsrach Evangelical Church |
|---|---|---|

“እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ” ሉቃስ 2:10




“Pray that ye enter not into temptation”. Luke 22:40-41

| Chicago Yemsrach Evangelical Church<br>4455 N. Seeley Avenue<br>Chicago, IL 60625 | መደበኛ ፕሮግራሞች<br>እሑድ 1:30 p.m. -- 4:30 p.m.<br>አርብ 7:00 p.m. -- 9:00 p.m. |
|---|---|
| **August 11, 2019** | **ነሐሴ 05 ፣ 2011 ዓ.ም.** |

## የእለቱ አገልግሎት መርሃ-ግብር

ጸሎት ........................... ወንድም ጌቱ ጳውሎስ

አምልኮ......................... የቤተ ክርስቲያን የአምልኮ ቡድን

ፕሮግራም መሪ ............ ዶር. ተረፈ አንሼቦ

ቃል .............................. መጋቢ ሐይሉ ውብሸት

ማጠቃለያ .................... ፕሮግራም መሪ

## የሳምንቱ ጥቅስ

" "ምንም እንኳን በለስም ባታፈራ ፡ በወይንም ሃረግ ፍሬ ባይገኝ ፡ የወይራ ሥራ ቢጎድል ፡ እርሾችም መብለን ባይሰጡ ፤ በጎች ከበረቱ ቢጠፉ ፤ ላሞችም በጋጡ ውስጥ ባይገኙ ፡ እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል ፡ በመድኃኒቴ አምላክ ሐሤት አደርጋለሁ።" (ዕንባቆም 3፡17-18)

| የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች | | |
|---|---|---|
| መሪ | ቀን | አድራሻ |
| ወ/ም አያሌው አስፋው | ማክሰኞ | **5030 N. Marine Dr., Chicago, IL 60640** |
| እህት ሰናይት ከበደ | ማክሰኞ | **7319 N Oakley Ave, Chicago, IL 60645** |
| ወ/ም ጌቱ ጳውሎስ | ማክሰኞ | **7200 N. Ridge Ave., Chicago IL 60660** |
| ዶ/ር ተረፈ አንሼቦ | ማክሰኞ | **7526 N. Ridge Blvd., Unit #3W, Chicago IL 60645** |
| ወ/ም ረድኤቱ ካሳ | ሃሙስ | **7252 W. Everell Ave., Chicago, IL 60631** |
| ወ/ም ሳሚ ኃብተየስ | ሰኞ | **9107 Laramie St. Skokie, IL 60077** |
| ወ/ም ዮናስ ባህሩ | ማክሰኞ | **5523 N. Kenmore Ave., Chicago, IL 60640** |
| | | |

## መልዕክተ ሰንበት

ወ/ም ብርሃኑ አንበሴ

### ተቀብተናል

*"በክርስቶስም ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሄር ነው...." 2ቆሮ. 1፡21-22*

*"እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል ሁሉንም ታውቃላችሁ....ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ ይኖራል ማንም ሊያስተምራችሁ አያስፈልጋችሁም...." ዮሓ. 2፡20-22 እና 27*

አብዛኛውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን አካባቢ "እከሌ የተቀባ አገልጋይ ነው....ወዘተ" የሚለው ቃል የተለመደ ነው። ሰዎች መቀባትን ለተወሰኑ ጥቂት ገለሰቦች እንጂ ለራሳቸው የተገባ አድርገው አያስቡትም። እንዲሁም ተቀብታችኋል የተባሉትም ግለሰቦች እራሳቸውን ከሌሎቹ ምእምናን የተለዩ በማድረግ ልዩነትን ሲፈጥሩ ይስተዋላል። ይሁንና ከላይ የተመለከተው የመጽሃፍ ቅዱስ ክፍል ዛሬ በዚህ ዘመን እኛ ስለተቀቡት ሰዎች ከምናወራው እጅግ የተለየ ነው።ይህም በክርስቶስ የሆነ አማኝ ሁሉ ከቅዱሱ ቅባት የተቀበለ ወይም የተቀባ እንደሆነ እና ቅባቱ በ እርሱ እንደሚኖር ነው። ዛሬ ባለችው ቤተ ክርስትያን ያለው ከላይ የተጠቀሰው አመለካከት ግን የተወሰደው ቀድሞ በብሉይ ኪዳን ከነበረው የመቀባት ሂደት ነው።

እርግጥ ነው በቀድሞው ኪዳን እግዚአብሄር በእስራኤል ሕዝቦች መካከል የሚያገለግሉትን ካህናት እና ሕዝቡን የሚመሩትን ነገስታት ብቻ በመምረጥ እንዲቀቡ ያዝዝ ነበር። ለምሳሌ ለክህነት ከአሮንና ከልጆቹ እንዲሁም ከሌዋዉያን በስተቀር ማንም ሰው መቀባት አይችልም ነበር። በተጨማሪም በ እግዚአብሄር ማደሪያ ውስጥ ለአገልግሎት የሚውሉ እቃዎች ሳይቀሩ እንዲቀቡ እግዚአብሄር አዝዞአል (ዘጸ. 30፤ 25-33)። ሌላው እግዚአብሄር እንዲቀቡ የሚያዘው ነገታትን ነበር። ሕዝቡን የሚያወጡና የሚያገቡትን፤ ከጠላቶቻቸው የሚታደጉአቸውን ነገስታት እግዚአብሄር ከመረጠ በኋላ በነቢያቱ አማካይነት እንዲቅቡ በማድረግ በሕዝቡ ላይ እንዲሾሙ ያዝዝ ነበር። ይህ ደግሞ ሰዎችን ለክህነትም ሆነ ለንግስና ብቁ የሚያደርጋቸው ቅባቱ ብቻ እንደሆነ ያመለክታል። ስለዚህ በቀድሞው ኪዳን ዘመን እግዚአብሄር በመቅደስ የሚያገለግሉትን ካህናትም ሆነ ህዝቡን የሚመሩትን ካህናት ለራሱና እራሱ በመለየት እንዲቀቡ ያዝዝ ነበር። ይሁንና በአዲስ ኪዳን ይህ ሂደት ተቀይሮ የክህነቱም ሆነ የንግስናው ቅባት ከየትኛውም ነገድና ዘር ቢሆንም በክርስቶስ ኢየሱስ ለሆነ ሁሉ ተሰጠ።

እንግዲህ ወገኖች ከላይ በጥቅሱ ውስጥና በመልክቱ እንደተመለከታችሁት እንደ ብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሄር የተወሰኑ ሰዎችን ብቻ ለይቶ በነብያቶቹ አማካይነት በዘይት የቀባ ሳይሆን የተቀባውን ክርስቶስ ኢየሱስን በመቀበላችሁና መንፈስ ቅዱስ በእኛ በመሆኑ ምክንያት ቅዱሱ ቅባት በውስጣችን ነው፤ ወይም ተቀብተናል ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን በተቀቡ ሰዎች ላይ ቅባቱ የሚያመጣው የራሱ ተጽዕኖና ሥራ እንደነበረው ሁሉ በአዲስ ኪዳንም በተቀባነው በእኛ ህይወት ለእግዚአብሄር በተሰጠንለትና በቅድስናችን መጠን ቅባቱ እየተገለጠ የሚሰራው የራሱ የሆነ ተግባር እንዳለው በሚቀጥለው ጽሁፍ የምንመለከተው ይሆናል።